# ጋዜጣዊ መግለጫ

የአሜሪካ ኤምባሲ፤
አዲስ አበባ፤ ኢትዮጵያ
2015/08

ለተጨማሪ መረጃ ቀጥሎ በተመለከተው ቁጥር ይደውሉ፡-011-130-7033
ድረ-ገጽ፡- http://ethiopia.usembassy.gov

## የአሜሪካ ዓለም አቀፍ ልማት ኤጀንሲ በደቡብ ብሔር፣ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልል አምስት ጤና ጣቢያዎችን አስገነባ

*ኤጀንሲው ያስገነባቸው እነዚህ አዳዲስ ጤና ጣቢያዎች ከ250,000 በላይ ለሚሆኑ ታካሚዎች አገልግሎት የሚሰጡ ይሆናሉ*

**ሲዳማ፣የደብብሕክ፣ኢትዮጵያ፤የካቲት 30 ቀን 2007 ዓ.ም**.፡-የአሜሪካ ዓለም አቀፍ ልማት ኤጀንሲ(USAID) በደቡብ ብሔር፣ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልል ያስገነባቸውን የመጀመሪያዎቹን አምስት ጤና ጣቢያዎች ለክልሉ የጤና ቢሮ በዛሬው ዕለት አስረከበ፡፡ጤና ጣቢያዎቹ በሲዳማ ዞን(ጃራዳዶ)፣በጉራጌ ዞን (ዋቾ)፣ሀዲያ ዞን (መሃል ጃርሶና ሲዲያ)፣እንዲሁም በስልጤ ዞን(ኡዳሳ) የተገነቡ ሲሆን፤የጤና ተቋማቱ ለኤች አይ ቪ የተጋለጡ፣ከቫይረሱ ጋር የሚኖሩትን ጨምሮ ከ250,000 በላይ ለሚሆኑ ታካሚዎች አገልግሎት ይሰጣል ተብሎ ይጠበቃል፡፡

የአሜሪካ ዓለም አቀፍ ልማት ኤጀንሲ ከፕሬዚዳንቱ አስቸኳይ የኤድስ እርዳታ ዕቅድ(PEPFAR) ባገኘው ድጋፍ ተቋማቱን በኢትዮጵያ የጤና መሠረተ ልማትን ማስፋፋት በተሰኘው መርሀ ግብሩ በኩል አስገንብቷል፡፡ መርሀ ግብሩ ኢትዮጵያ አዳዲስ የጤና ተቋማትን በመገንባትና ለነባሮቹ እድሳት በማድረግ በሀገሪቱ በሚገኙ ዋና ዋና ክልሎች ለወሊድ አገልግሎትና በኤች አይ ቪ የተጠቁ ዜጎች ህክምና የሚያገኙባቸው ንጹህና ምቹ ማዕከላት እንዲኖሯት እገዛ የሚያደርግ ነው፡፡

በኢትዮጵያ የአሜሪካ ዓለም አቀፍ ልማት ኤጀንሲ ዳይሬክተር ዴኒስ ዌለር በሲዳማ ዞን በጃራዳዶ የሚገኘው ጤና ጣቢያ የምረቃ ሥነ ሥርዓት ላይ ባደረጉት ንግግር፡-“ ዛሬ የተደረገው ርክክብ ኢትዮጵያ የኤች አይ ቪ ወረርሽኝ በመዋጋትና የሰዎችን ህይወት በማዳንና ተጨማሪ ሰዎች እንዳይያዙ ለማድረግ በዓለም አቀፍ ደረጃ ለምታደርገው ጥረት የተሰጣትን ዕውቅና ለማስቀጠል ያለንን ቁርጠኝነት ያሳያል” ብለዋል፡፡

በመርሀ ግብሩ በኩል የአሜሪካ ዓለም አቀፍ ልማት ኤጀንሲ 10 የመድኃኒትና የሌሎች ህክምና መሣሪያዎች ግምጃ ቤቶችን ያስገነባ ሲሆን፤ሌሎች አምስት የጤና ጣቢያዎችንም አሳድሷል፡፡ በተጨማሪም በአዲስ አበባ ብሔራዊ የደም ባንክ የማስገንባት ዕቅድም አለው፡፡

የአሜሪካ መንግሥት የፕሬዚዳንቱ አስቸኳይ የኤድስ እርዳታ ዕቅድ ግንባር ቀደም ተጠቃሚ የሆነችው ኢትዮጵያ፤በአሜሪካ ዓለም አቀፍ ልማት ኤጀንሲ፣በአሜሪካ የበሽታዎች መቆጣጠሪያና መከላከያ ማዕከል፣በመከላከያ ሚኒስቴር፣በሰላም ጓዶች፣እንዲሁም በአሜሪካ የውጭ ጉዳይ መሥሪያ ቤት የሥነ ህዝብ፣የስደተኞችና የስደት ጉዳዮች ቢሮ ከሚመሩ ዘርፈ-ብዙ የኤች አይ ቪ ፕሮግራሞች ድጋፍ ታገኛለች፡፡ በፕሬዚዳንቱ አስቸኳይ የኤድስ እርዳታ ዕቅድ በኩልም የአሜሪካ መንግሥት የኢትዮጵያ መንግሥት እ.ኤ.አ. ከ2005 ጀምሮ አዲስ በኤች አይ ቪ የሚያዙና በኤድስ የሚሞቱ ሰዎች ቁጥር በግማሽ መቀነስ እንድትችል ከፍተኛ የአቅም ግንባታ ሥራ ሠርቷል፡፡

###